የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

# የሕዝባዊ ስብሰባ ጥሪ በጀርመን - ኑርንበርግ ከተማ

ዛሬ ሀገራችን እና ሕዝባችን የሚገኙበት ሁኔታ ከመቼውም በበለጠ እጅግ አሳዛኝ አስጨናቂና አደገኛ መሆኑ በገሃድ የሚታይና የሚታወቅ ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ የሆነን ሁሉ ክፉኛ የሚያሳስብ እንደሆነ ግልፅ ነው። በተለያዩ ጊዜያትና አካባቢዎች የተደረጉና አሁንም ድረስ በቀጣይነት እየተካሄዱ ያሉ ከቀዬ የማፈናቀል እርምጃዎች የሚያመላክቱት ይህንኑ አስጊ ሁናቴዎችን ነው። ይህ ሁናቴ በነዚሁ ክፍሎችና ኃይሎች በተባበረና በተጠናከረ ትግል እንዲገታ ካልተደረገ ኢትዮጵያ እንደ ኢትዮጵያዊነቷ ለመቀጠል፡ ሕዝቧም በአንድነት አብሮ ለመኖር ያላቸው እድል እየመነመነ እንደሚሄድ ይታመናል።

ኢሕአፓ ከዚህ አደገኛና አሳሳቢ አዙሪት ሕዝብን ለመታደግ ባለፉት 22 አመታት ሳያቋርጥ በጽናት እየታገለ የበኩሉን አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል። ይህንን አስመልክቶ በጊዜያዊ የፖለቲካ፡ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁናቴ ላይ በመመርኮዝ „**ምን መደረግ አለበት**?“ ለሚለው ጥያቄ ከኢሕአፓ አመራር ጋር በጀርመን ሀገር ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያዊያን ጋር የኃሳብ ልውውጥና ውይይት ብሎም የሀሳብ አንድነት ለመፍጠር የሚቻልበትን ዘዴ ለመቀየስ ይቻል ዘንድ አንድ ታላቅ ስብሰባ በኑርንበርግ ከተማ ተዘጋጅቷል።

ስለሆነም ከታች በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በዚህ የውይይት ስብሰባ ላይ ተገኝቶ በመፍትሄው ፍለጋ የበኩሉን አስተዋፅዖ እንዲያበረክት በጀርመን የምንገኝ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች የከበረ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**ቦታ፡ Wartburgstraße 18 Nürnberg 90491**
**ቀን፡ June 22 2013(22/06/2013)**
**ሰዓት፡ 12:00-18፡00**

ወደ ስብሰባው ቦታ ለመምጣት በሕዝብ ትራንስፖርት ለምትጠቀሙ ከኑርንበርግ ዋና ባቡር ጣቢያ U2 ወደ ኤርፖርት አቅጣጫ የሚጓዘውን በመያዝ እስከ **Nord Ost Bahnhof** ተጉዘው ይወርዱና **Leipziger Straße** ወይም **Kiesling Straße** ይዘው በእግር ሲጓዙ የስብሰባውን ቦታ ያገኙታል። በመኪና ለሚመጡ የሚከተለዉን አድራሻ **Wartburgstraße 18 Nürnberg 90491** በመስጠት በቴክኖሎጂው ይጠቀሙ።

ለበለጠ መረጃ፡ 015214818081፣ 015211408316፣ 015210249776፣ 015211613665፣ 017825998578